# ቁዘማ፡- የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ

ፈቃደ አዘዘ

## 1. መግቢያ

ስለሕይወት ብዙ ነገር የምንማረው÷ በአካባቢያችን ያለውን "ኔቸር"ን ("ተፈጥሮ"ን[1]) በመመልከት÷ በመስማት÷ በመንካት÷ በማሽተት÷ በማጣጣምና÷ በሌሎች ስሜት-ዘለል (extra sensory) በሆኑ መንገዶች በየፊናችን በመረዳት ነው ማለት ይቻላል:: ለምሳሌ ጥንት እንስሳትን÷ እፀዋትን÷ ተራሮችን÷ ወንዞችን÷ ሰዎችን÷ ወዘተ.፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ እራሱ ሰውልጅ[2] (humankind) የሰራቸውን ልዩ ልዩ እቃዎችን÷ ህንፃዎችን÷ መንገዶችን÷ መሳሪያዎችን እና፤ ዛሬ ደግሞ ልዩ ልዩ የተራቀቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶቹን እና አብረዋቸው የመጡትን የአኗኗር ስርዓቶችና ዘይቤዎች በማየትና በመከተል ስንማር የኖርን÷ ዛሬም የምንኖር ይመስላል:: ሰውልጅ÷ መጀመሪያ ተፈጥሮን ከመቅዳት እና ከተፈጥሮ ጋር ከመታገል እየተማረ፤ በኋላ ደግሞ እራሱ አስቦ የሰራውን ቁሳዊና ኅሊናዊ ዓለም ከመቅዳትና መልሶም ከእርሱ ፍጡራንና ከውጤቶቻቸው ጋር በመታገል የኖረ ይመስለኛል:: ይህ በሩጫ የተሰነዘረ ሃሳብ÷ ከሞላ ጎደል ትክክል ከሆነ ስለ ንባብ ባህል ምንነት የምናደርገውን የዛሬውን ውይይታችንንም ከዚህ አጠቃላይ እውነታ ጋር አያይዘን ልንጀምር እንችላለን ማለት ነው:: የንባብ ባህል እንደብዙው ሌላ በጎ እና በጎ ያልሆነ ነገር ከቤተሰብና ከአካባቢ ይጀምራል ብዬ አምናለሁ:: ከዚህም በፊት በተለያዩ አጋጣሚዎች በፅሁፍና በንግግር እንደገለፅሁት÷ የማንኛውም ጥሩ ወይም መጥፎ ነገር ችግኝ ማፍያ ቤተሰብና ጎረቤት (አካባቢ)÷ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ትምህርት ቤት÷ የብዙኃን መገናኛ (በተለይ በእኛ ሀገር ደግሞ÷ ሬድዮና ቴሌቪዥን) እና ማኅበረሰብ ናቸው:: በዚህ ሁሉ ውስጥ መንግስት የሚባለው የአስተዳደር መዋቅርና ስርዓት

---

[1] "ተፈጥሮ" የሚለው ቃል "ፈጣሪ አለ" "ተፈጣሪ አለ" የሚሉ ሃሳቦችን ይጠራል:: እኔ ደግሞ የዚህ የዓለማችን አመጣጥ እንደብዙዎቻችን ግራ እንደገባኝ አለ:: ቁርጥ መልስ የለኝም÷ ወይም አላገኘሁም:: ጥቂት የማይባሉ ሰዎች መረጃ ያጡበትን ነገር በእምነት ሲተኩ ይታያሉ:: ይህንን ማድረጋቸው ሁሉንም ያርካ አያርካ÷ ለሁሉም ሰላምና እንቅልፍ ይስጣቸው አይስጣቸው ግን አላውቅም:: እኔ የመረጥኩት "ኔቸር" በሚለው÷ የፈጣሪና የተፈጣሪ ሃሳብን ሳያስተጋባ ነገሮቹን ብቻ የሚጠራ በመሰለኝ ቃል መገልገልን ነው:: ብዙ ጊዜ ግን÷ የምናገር ወይም የምፅፍበት ሁኔታ እያጣደፈኝ÷ ወይም ደግሞ የአድማጮቼ ዓይነት እየገፋፋኝ "ተፈጥሮ" ስል እገኛለሁ፤ ወደፊትም ልገኝ እችላለሁ:: ለጊዜው ምርጫዬ "ኔቸር" ነው:: ወደፊት÷ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎቹ ባንዱ ውስጥ ምትክ ቃል አገኝ-አገኝ ይመስለኛል::

[2] ረቂቁ ኢትዮጵያዊ ገጣሚ÷ አቶ ሰይፉ መታፈሪያ "ዘራሰብ" ይሉታል::

ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ዝቅተኛም ከፍተኛም፥ በጎም እኩይም ሚና ሲጫወት ይታያል።

ከዚህ በላይ በተናገርኳቸው ቃላት፥ ሀረጎችና ዐረፍተነገሮች ውስጥ የጠቃቀስኳቸው ሃሳቦች እምቅ ናቸው። ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች በውስጣቸው የያዙ መሆናቸውን በውል እገነዘባለሁ። ስለዚህም፥ እነዚህን ዝርዝሮች፥ በዝርዝር እና በጥልቀት፥ በመረጃ ላይ ተደግፈን መሰረታዊ ጥናት ማኪያሄድ አለብን። ይህንን ሳናደርግ የምንናገረው ብዙው ነገር ከግል አስተውሎትና ከግል ልምድ የመነጨ አስተያየት ብቻ እንደሆነ ከወዲሁ ማሳሰብ እወዳለሁ። ይህንን የምለው ዛሬ እንድወጣ ከተሰጠኝ ኃላፊነት ለመሸሽ ሳይሆን በየልማትና እውቀት መስኩ መሰረታዊ ጥናትን የማኪያሄድን አስፈላጊነት ለአድማጮቼ (ለአንባቢዎቼ) አበክሬ ለማሳሰብ ነው።

በሀገራችን፥ ብዙ ነገር ከስር ከመሰረቱ ጀምሮ ሲጠና አላየሁም። ጊዜም ገንዘብም የሚገኘው ጥቂት ዓመታት ወስዶ በየሙያ መስኩ በእቅድ እና በእውቀት ለሚደረግ መሰረታዊ ጥናት ሳይሆን በየጊዜው በየሰበቡ ለሚቀሰቀስ ለወቅታዊ የመረባረብ ስራ ይመስለኛል። ከአፄው ዘመን ጀምሮ እኔ ያየኋቸውን መንግስታት ከሚያመሳስሏቸው እጅግ ብዙ ነገሮች መሀከል አንዱ ሁሉንም ነገር (የእውነት ስልጣንን በሐቅ ከማጋራት በስተቀር ማለት ይቻል ይመስለኛል) በመረባረብ እንስራ እያሉ መለፈፋቸው ይመስለኛል። እርግጥ ጭፍን መረባረብን እንደልማትና የኑሮ መርሕ የመውሰድ ልምድ ከመንግስት መንግስት በቅብብሎሽ በሚመስል መንገድ እየተስፋፋና እየተባባሰ የሄደ ይመስላል። መቼና እንዴት እንደሚቆም የሚያመለክት ፍንጭ የለም። እኛም፥ በተለይ ተማርን የምንባል ትኙ ዜጎች፥ ይህ ነገር ተደጋግሞ ስለተነገረን ቆም ብሎ ማሰብና ማሰላሰልን በጭፍን መረባረብ ቀስ-በቀስ እየተካን የመጣን ይመስላል። ብዙ ጊዜ፥ በመረባረብ መንገድ ስለመስራት፤ በመረባረብ የቀበሌ፥ የከተማና የሀገር ፀጥታ ስለማስከበር፤ በመረባረብ ኤች.አይ.ቪ./ኤይድስንና ወባን ስለመዋጋት፤ በመረባረብ የከተማውን ፅዳት ስለመጠበቅ፥ በመረባረብ ጫካዎችን ስለመጠበቅና ስለማልማት፥ በመረባረብ ትምህርት ቤቶችን መስራት ወይም የትምህርትን ጥራት ስለመጠበቅ፥ ወዘተ. ሲነገር እየሰማሁ ነው ያደግሁት። ዛሬ፥ የንባብ ልምድን በመረባረብ ስለማሳደግ ባንነጋገር እወዳለሁ።

ይህንን ስል፥ የሕዝብ ተሳትፎ አይጠራ፥ አይቀስቀስ ማለቴ አይደለም። እኔ የምለው፥ መጀመሪያ የየሙያው (ማለትም፥ የትምህርት፥ የጤና፥ የፀጥታ፥ የፅዳት፥ የደን ወዘተ.) ባለቤት በሀገር ደረጃ በባለሙያዎች ተዋቅሮ፥ በእውቀትና በጥናት ላይ ተመስርቶ

በተነደፈ እቅድና ስርዓት ተደግፎ÷ ይህንን እንቅስቃሴውንም ለዜጎቹ በይፋ አሳውቆ÷ የእነርሱን ሃሳብና ምክር ሰብስቦ÷ የአቅሙን ያህል መስራት ይጀምር፤ የስራውንም ሂደት ደረጃ በደረጃ ያስታውቅ ነው፡፡ ይህንን ያወቁ ዜጎች÷ የእቅዱን ግብ መምታት ለማፋጠን በግልና በቡድን የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ ቢረባረቡ በጣም ከሚደሰቱት መሀከል አንዱ እኔ ነኝ፡፡ የምደሰተው÷ ሁሉም ነገር በእውቀት÷ በስርዓት እና በእቅድ ውስጥ ሲከናወን አንድ ስራ የት÷ መቼ÷ ተጀምሮ፤ የት÷ መቼ እንደደረሰ በግልፅ ለመከታተል ስለሚቻል ነው፡፡ እስከዛሬ ያለው የእንረባረብ መፈክር÷ በእኔ አስተያየት÷ ሙሉ በሙሉ ቅን አይመስለኝም፡፡ ከዚህም አልፌ÷ ፈካሪዎቹ መንግስታት ከሆኑ ብዙ ጊዜ የሚፈክሩት÷ እራሳቸውን በስልጣን ላይ ለማቆየት ሲሉ ነው ብል እወዳለሁ፡፡ የሚፈክሩት ግለሰቦችና አንዳንድ የሲቪክ ድርጅቶች ሲሆኑ ደግሞ÷ ጥቂት የማይባሉት የሚፈክሩት ከግል ጥቅማቸው ጋር ሲያያዝ እየመሰለኝ መምጣቱንም መግለፅ እሻለሁ፡፡ ይህንን የምለውም ካንድም ሁለቴ የደረሰብኝን እና በሌሎች ደረሰ የተባለውን ይዤ ነው፡፡ እርግጥ÷ ስልጣን-ተኮር የሆኑ መንግስታት÷ ጥቅም-ተኮር የሆኑ ግለሰቦች እና ቡድኖች በዓለማችን እየበዙ ስለሆነ ይህ መሆኑ አያስደንቅም፡፡ ነገር ግን ከመረባረቡ መፈክር በስተጀርባ ያለው ዋናው ቁምነገር የግል ጥቅም ከሆነ የመረባረቢያ መፈክሩ ዓላማ ሩቡ ቀርቶ ከአስር አንዱም አይከናወንም፡፡

ትኩረቱ እስልጣንና እግል ጥቅም ላይ ከሆነ÷ ስለየሙያው በቂ እውቀት የሌላቸው ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች÷ በየዘመኑ÷ ሙያ የሚጠይቅን ስራ እንዲሰሩ መመደባቸው ይቀጥላል ማለት ነው፡፡ በማያውቁት ወንበር ላይ በመመደባቸው (ትክክለኛው ቃል "በመወዘፋቸው" ይመስለኛል) ምክንያት ጠብ የሚል ነገር ሲጠፋም የመረባረብን ሙሾ በተለያየ የጣርና የጥድፊያ ዜማ ማዥጎድጎድ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡ ነገሮች ከመሰረታቸው ሳይጠኑ÷ እንዲህ እንደዛሬው እየተገናኙ በብዙ ርእሶች ላይ ተነጋግሮ መለያየት ብዙ መሰረታዊ ፍሬ ሳይሰጥ የቆየው÷ ቢያንስ የዛሬ 70 ዓመት ገደማ አባቶቻችን ያነሱትን ከንባብ ጋር የተያያዘ ፕሮብሌም÷ በመሰረቱ ብዙም ባልተለወጡ ቃላትና ሀረጋት ዛሬም የምናወሳው÷ ፕሮብሌሞችን በያዝ ለቀቅና በግብታዊ የመረባረብ መፈክሮች ማስተናገድን ትዳራችን ብለን ስለያዝን ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከንባብ ጋር አያይዘን የምናነሳው ብዙው ፕሮብሌም ከዚህ በላይ ከጠቃቀስኳቸው ከብዙ የሀገር ጉዳዮች አያያዛችን ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ይህንን ለመንደርደሪያ ያህል ከተናገርኩ በኋላ÷ እመነሻዬ ላይ÷ የንባብ ልምድ ከቤተሰብና አካባቢ ጋር ይያያዛል ብዬ ነበርና ወደዚያ ልመለስ፡፡

## 2. ቤተሰብ

የንባብ ባህል ከቤተሰብና ካካባቢያችን ከምንቀስመውም ነው የሚጀምረው:: የቤተሰብ÷ የዘመድ÷ የጎረቤት ተፅእኖ ወዘተ. ከሌሉ አንድ ልጅ የማንበብ ልምዱን ቀርቶ የማንበብ ፍላጎቱን ከየት ያመጣዋል? ብዙ ጊዜ÷ እቤት ውስጥ የሚያነብና የሚፅፍ ሰው ካለ እርሱን ተከትሎ የሚያነብና የሚፅፍ ሰው ሊኖር የሚችልበት እድል ወይም አጋጣሚ ሰፋ ይላል:: ባጭሩ ለማስረዳት÷ ጥሬ ስጋ መብላት በተለመደበት ቤት ብዙ ጥሬ ስጋ በላተኞች ማፍራት አይቸግርም:: ችግሩ ጥሬው ስጋ ሁሉም ቤት ስለማይገኝ የመልመድ እድል ያላቸው ሰዎች ቁጥር የተወሰነ መሆኑ ላይ ነው:: ንፅፅሩ መቶ በመቶ ይሰራል ባይባልም ፅሁፍም እሁሉም ቤት የለም:: መቼም የጥሬ ስጋን ያህል እንደሌለ ግልፅ ነው::

## 3. ቤተ ሃይማኖትና የቄስ ትምህርት ቤት

ስጋው ገንዘብ ባላቸው ሰዎች ዘንድ እንደሚገኝ ሁሉ ፅሁፍም ቤተሰብን ተጠግቶ ሳይሆን የነበረው÷ ባብዛኛው ቤተ ሃይማኖቶችን ተጠግቶ ነበር በኢትዮጵያ የቆየው:: ወደዜጋው ቤት ለመግባት ደፍሮ ነበር ማለት አይቻልም:: በተለይ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ትምህርት ቤቶች ጋር ተያይዞ ግን ለረዥም ዓመታት ቆይቷል:: እዚያም ቢሆን ሁሉም አያነብም÷ ሁሉም አይፅፍም[3]:: ኢትዮጵያም ብትሆን ረዥም የፅሁፍና የስነፅሁፍ ታሪክ አላት የምትባለውን ያህል ማንበብና መፃፍ የሚችል ሕዝብ ኖሯት አያውቅም:: የቤተክህነት ትምህርትም የቃል ትምህርት ይበዛበታል::

የቄስ ትምህርት ቤቶች ሁኔታም የማንበብ ልምድን የሚኮተኩት ነበር ማለት አይቻልም:: በሹሮ ሜዳና በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት መሀከል ከነበሩት "የቄስ ትምህርት ቤቶች" እኔ የተማርኩባቸው ሁለት ሶስት ይሆናሉ:: እማስታውሰው ሀ-ሁ መቁጠርን÷ አቡጊዳና መልእክተን መውረድን ነው:: መምህሩ የያንዳንዳችንን ንባብ ወይ አጠገባችን መጥተው ወይም ደግሞ እተቀመጡበት ሆነው እያደመጡ ስንሳሳት በቃላቸው ያርሙ ነበር:: ነፍስ ካወቅሁ በኋላ÷ በተለይ ስለንባብና ስለፅሁፍ ማሰብ ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ÷ የሁላችንንም ስህተት በቃላቸው ማረማቸው ሁላችንንም ስላስገረመ÷ እናዳብር የነበረው የማንበብ ክሂላችንን ሳይሆን እንደርሳቸው በቃል የመያዝን ክሂል ይመስለኛል:: በቃል የመያዝን ክሂል ማዳበሩ የሚደነቅ ቢሆንም÷

---

[3] ባህሉ÷"አይጽፍ ደብተራ÷ ክንፍ የለው አሞራ" (ደ.ተ.ወ.÷ ገፅ 336) ሲል የጽሕፈት ባህል የት እንዳለ እየጠቆመ ነው:: የማይፅፍ ደብተራ እና ክንፍ የሌለው አሞራ አንድ ናቸው ነው የሚል:: ክንፍ የሌለው አሞራ አይበርም:: ሳይበር መኖር ይችላል ማለት ያስቸግራል:: ካልፃፈ÷ የደብተራውም እጣ ተመሳሳይ ይሆናል ነው የሚል ምሳሌው:: ይህ ምሳሌያዊ ንግግር መጀመሪያ በተነገረበት ጊዜ÷ ጽሕፈትና ንባብ ተራው ሕዝብ ዘንድ አልደረሰም ነበር ማለት ሳይቻል ይቀራል?

የትምህርት አሰጣጡ ማንበብን የሚያለማምድና የንባብ ፍቅርን የሚኮተኩት ነበር ለማለት ያስቸግራል ያልኩት አንድም ለዚህ ነው።

ረቂቁ ቅኔም፥ ለረዥም ዓመታት ይደረስ፥ ይከወን እና ይቀረስ የነበረው በቃል ነበር። ዛሬም ቢሆን በየቀኑ በቃል ተደርሶ፥ በቃል ተከውኖ፥ "የቅኔ ቋንጣ የለውም" በሚል መፈክር ጭምር እየተበረታታ በፅሁፍ ሳይቀረስ የሚቀር ቅኔ ብዙ ነው። ረዥሙን የፅህፈት ታሪካችንን ስንቃኝም ተተርጉሞም ይሁን በእኛው ሰዎች ተደርሶ ጥንት የተፃፈው፥ ባብዛኛው በግእዝ ቋንቋ ሆኖ ይዘቱም ከሃይማኖትና ከመለኮት ጋር የተያያዘ ሆኖ ይገኛል። ስለየዘመኑ እለታዊ ኑሮ ተርታው ሰው በሚገባው ቋንቋ የተፃፉ፥ ፊደል የቆጠረው ሰው ስለራሱ ህይወት እያነበበ የማንበብ ልምዱን እንዲያዳብር የሚያግዙ ፅሁፎች እምብዛም አልነበሩም። በዚህ ላይ የማንበብና የመፃፍ ትምህርት እንኳን ጥንት ዛሬም በወጉ አልተስፋፋም። ስለዚህ እንኳን በጥንቱ የኢትዮጵያ ቤተሰብ ቀርቶ በዛሬው ቤተሰብም ውስጥ የማንበብ ልምድ አለ ማለት ጨርሶ አይቻልም።

እርግጥ፥ መፃፊያ ቀለምና ብራናው እንደልብ በማይገኝበትና ሲገኝም እጅግ ውድ በነበረበት ጊዜ የሚነበበው ነገር እራሱ ስላልነበረ ልምዱ ባይስፋፋ አይገርምም። ነገር ግን፥ ማተሚያ ቤቶች እየተቋቋሙና አንፃራዊ በሆነ መንገድም እየተስፋፉ ሲሄዱ፥ የጅማ ትምህርትም (mass education) በተለይ ከዘመነ ደርግ ጀምሮ እየተስፋፋ ሲሄድ፥ የማንበብ ልምድ ለምን አብሮ አልተቋቋመም? ለምንስ አልተስፋፋም? እነዚህን መነሻ አድርጎ ሌሎች ጥያቄዎችን ማስከተል ይቻላል። ነገር ግን ወደዚያ ከማምራት ስለ ንባብ የሚሰነዝሩ አንዳንድ ባህላዊ አመለካከቶችን እንመለከት።

## 4. ባህላዊ አመለካከት

ጊዜ ቢኖር፥ መጀመሪያ ከባህሉ ( ለምሳሌ፥ ከትምህርት ቀመስ ስነቃሉ፥ ከምሳሌያዊ ንግግሩ፥ ከእለት ተእለት ወጉ፥ ወዘተ.) የሚመነጩ የንባብን ባህል የሚያሞካሹም ሆኑ የሚያንኳስሱ አስተያየቶች መኖር አለመኖራቸውን ለመመርመር እሞክር ነበር። ዛሬ፥ ያንን ለማድረግ ስለማልችል፥ በመዝገበ ቃላት ልጀምር።

በደስታ ተክለወልድ (ደ.ተ.ወ.) መዝገበ ቃላት "ንባብ" የሚለው ቃል በብዙ ቅርፆች ቀርቦ ትርጉሙ ተሰጥቷል። አንዱን ፍች ቃል በቃል እጠቅስና በሌሎቹ ውስጥ የተደጋገመውን ፍች በእኔ አነጋገር አሳጥሬ አቀርባለሁ። "ንባብ፣ ከወርድ ንባብ በኋላ

ተማሪ እየጮኸና እያሰማ በፍጥነት የሚናገረው ከነቁጥ እስከ ነቁጥ ያለ የሚነሣና የሚወርድ የሚጠብቅና የሚላላ የግእዝ ቃል። ..." ነው ይላል (ገፅ 831)። ትኩረቱ ጮክ ብሎ ለሌሎች ማሰማት ላይ ነው። በለ-ኖሳስ ወይም ድምፁን ሳያሰማ በቀስታ ካነበበ ደግሞ "ደገመ" ይባላል (ገፅ 339)። ይህ በግል ጸሎት ጊዜ የሚደረግ ነው[4]። እገሌ "ሃይማኖተ አበው አንባቢ" ወይም ደግሞ "ፍታነገሥት አንባቢ ነው" የሚለውም የመጀመሪያውን ፍች፥ ማለትም ጮክ ብሎ ማንበብን፥ ተከትሎ ነው። "ንባብ ቤት"፥ "ንባብ ዐዋቂ"፥ "ንባብ ትምርት" (ወይም በግእዙ "ትምህርተ ምንባብ") ሲልም በዚሁ ፍች ላይ ተመርኩዞ ነው[5]። "አናበበ" ሲል ደግሞ መጻፍን ከመጻፍ ማስተያየትን ስለሚጠቅስ የተለየ ፍች ይይዛል። ይህ ሁሉ፥ እኛ ዛሬ ከምንወያይበት የንባብ ፍች ጋር አለመያያዙ ግልፅ ነው። ብዙው የተለየ ትምህርትንና እና ሙያን የሚያመለክት ነው።

እዚሁ መዝገበ ቃላት ውስጥ፥ "መጣፍ ገላጭ፤" ማለት "መጣፍ የሚገልጥ ጠንቋይ ደብተራ" (ገፅ 575) ማለት ነው። ልብ በሉ። ብዙ ጊዜ መፅሀፍ ለሚያነብ ሰው የሚሰጡት እኔ ተማሪ ሆኜ የማውቃቸው መጠሪያዎች አሉታዊና አግላይ የሆኑት "እጥቤዋ፥ ቀለሜዋ፥ ሸምዳጅ፥ ቀበኛው፥ መጽሐፍ አጣቢው፥ አሞ ወዘተ." የሚሉ ናቸው። ዛሬም እነዚህን የሚመስሉ መጠሪያዎች እንዳሉ አውቃለሁ። በዚህ ላይ መጽሐፍ አዘውትሮ የሚያነብን ሰው "ኧረ ዓይንህ ይጠፋል ተው!" ማለት፤ ከሰዎች ገለል ብሎ፥ እዛፍ ወይም ሌላ ጥላ ስር ለረዥም ጊዜ መጽሐፍ የሚያነብን፥ ማታ አምሽቶ ወይም ሌሊት ተነስቶ የሚያነብን ሰው "ኧረ መጋኛ ይመታሃል ተኛ! ምን ይጥቅመኛል ብለህ ነው!?" ማለት ያልተለመደ አነጋገር አይደለም። "እገሌ ድግምተኛ ነው! ተጠንቀቅ!" ሲባልም ንባብን ከምትኃትና ከጥንቆላ ጋር አያይዞ ማስፈራራት አለበት። እንደዚህ ዓይነቶቹ አነጋገሮች፥ እንኳን ስለንባብ ባህል ምንም ያላሰበውን ሰው ቀርቶ "የንባብን ባህሌን ላዳብር!" ብሎ ታጥቆ የተነሳውን እንኳ ያስፈራራሉ፥ እያመነታ እንዲኖር ያደርጋሉ። በቀላሉ የሚገፉ እንቅፋቶች አይደሉም ማለት ነው። ይህ ዛሬ ልንነጋገርበት የሚገባ አንድ ፕሮብሌም ይመስለኛል።

"ማንበብና ትምህርት የሚያስፈልገው ስራ ለመቀጠርና ለደሞዝ ወዘተ. ነው!" የሚለው ሃሳብ፥ "ትምህርት ልዩ ልዩ መንፈሳዊና ዓለማዊ መረጃ፥ ቁሳዊና ስነልቡናዊ እውቀት ማግኛ፤ ሰብእናን ኮትኩቶ ማሳደጊያም ወዘተ. ነው" የሚለውን ሃሳብ ያህል በተለይ በወጣቱና በማኅበረሰቡ ዘንድ አለመስፋፋቱም ሌላው እክል ነው። ብዙ ማንበብና

---

4 የ"ደጋሚ" አንዱ ፍች እና የ"ድግምታም"፥ የ"ድግምት" ፍች ግን ከአስማት፥ ከመሰሪ፥ ከዐዚም፥ ከመተት፥ ከጥንቆላ ጋር የሚያያዝ ነው።

5 ከንባብ ዓይነቶች አንዱ የሆነው "ወርድ ንባብ፤ እንደ ዐቢይ ንባብ የማይቀለጥፍ ጉት የሐዘን ንባብ" ነው (ገፅ 458)። በዚህ አገባብም ዛሬ እኛ የምንነጋገርበትን የ"ንባብ"ን ፍች ጨርሶ አያመለክትም።

ማወቅ÷ በከፍተኛ ትምህርት የታነፀ የሙያ እውቀት መጨበጥ እና÷ እኒህ ባለሙያዎችና ባለእውቀቶች በእለት ተእለት የኢኮኖሚ ኑሮ ውስጥ የያዙት ስፍራ አይመጣጠንም። በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ያላቸው ሚና÷ በስልጣን እርከን ውስጥ ያላቸው ጡንቻና ተሰሚነትም ተመጣጥነው ከመገኘት ይልቅ እጅግ ተራርቀው ነው የሚገኙት። በአጎጉራችን እና በሀገራችን÷ አገር ለመምራት÷ አገር ለማስተዳደር እና መልካም ኑሮ ለመኖር እውቀትና ትምህርት አስፈላጊ መሆኑ እየቀረ የሄደ ይመስላል። የሀገር መሪ÷ አስተዳዳሪና ባለስልጣን ለመሆን የሚያስፈልገው ዋና ችሎታ÷ ብዙ ጊዜ÷ ጉልበት ነው። ለአውራው ጉልበተኛ ያደሩ መምሰል÷ ስሜቱንና ግንባሩን እየተከተሉ ማስመሰል እና በጭፍን አድር-ባይነት ማደግደግ ደግሞ ሌሎቹ መንገዶች ይመስላሉ። በዚህም ምክንያት ለእውቀት÷ ለትምህርት እና ለንባብ የሚሰጠው ክብር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመነመነ የመጣ ይመስላል። በዚህ ውስጥ የንባብ ባህል እንዴት ይዳብራል? "ትምህርት ለሀገር ይጠቅማል! ትምህርት ያበላል! ትምህርት ያስከብራል! ወዘተ." ማለት እየቀረ "ከአስር ዲግሪ አንድ ግሮሰሪ" ማለት በሀገር ደረጃ ከገነነ፤ "የሚያበላው ባንድ የትምህርት ዓይነት እንደምንም ብሎ አንድ የሆነ ወረቀት÷ አንድ ዲፕሎም ወይ አንድ ዲግሪ ይዞ÷ አንድ የሚያበላ ቦታ ላይ በሆነ ዘዴ መቀመጥ ነው" የሚል አደገኛ መፈክር እየጎላ ከመጣ በዚህ ውስጥ የንባብ ልምድ መዳበሩ ቀርቶ የሀገሪቷ የትምህርትና የልማት አኪያሄድ እራሱ አደገኛ አቅጣጫ ውስጥ አይገባም? እኔ የሚገባ÷ የገባም ይመስለኛል።

ይህም ብቻ አይደለም። ሁኔታው የተማረውን ክፍል÷ እርሱንም ሆነ ሀገሩን እማይጠቅም የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ እንዲገባ ሊገፋፋው ይችላል። ሲጀመር መዝናኛ ሊመስል ይችላል። ቀስ እያለ ግን ጥሩ መደበቂያ÷ መሸሸጊያ እየመሰለ እያሳሳቀ ሊወስድ ይችላል። መጀመሪያ ስለሀገር ማሰብን÷ እየተነጫነጩ ከአእምሮና ስሜት ውስጥ በመጠጥ÷ በቁርጥ እና በወሲብ መንግሎ ማውጣት ይመጣል። ከዚያ የሙያ ግዴታ ጭምር ይረሳል÷ ችላ ማለት ይስፋፋል። "ነፃ ኢኮኖሚ" በሚባል አጉል መፈክር እየታጀቡ በግል ጥቅም ማሳደድ መሰልጠን ይደራል። ይህንን ሁሉ ደስ እያላቸው የሚያደርጉ እንዳሉ ሁሉ ተስፋና ርእያቸው (their vision) ከውስጣቸው ተሟጦ ስላለቀባቸው በእልህ ጭምር÷ እያዘኑም÷ እየተቃጠሉና እየጨሱም የሚፈፅሙ ያሉ ይመስለኛል። ዋናው ቁምነገር የነዚህ ሁሉ ድምር÷ ለራሳቸው ለግለሰቦቹ÷ ላስተማረን ለሀገሪቱ ደኃ ሕዝብ እና በጅምላ ለምንድሰኩርለት የሀገር ልማት የፈየደው ነገር አለመኖሩ ነው። የዚህ ጉዳይ ዝርዝር ብዙ ነው። ስለዚህ ከንባብ ጋር በሚገናኝበት መንገድ ላይ በቶሎ ላተኩር። ማያያዣ ግን ያስፈልገኛል።

## ቁዘማ፡- የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ

በእውነት፥ ከአፄው ዘመን ጀምሮ እየተስፋፋ የመጣ የተማረው ሰው ዋና የመዝናኛ መንገድ በምግብ፥ በመጠጥ እና በወሲብ ላይ እያተኮረ የመጣ ይመስላል። ይሄ ነገር ማንኛችንንም አይምርም። ቢያንስ ብዙዎቻችንን ይነካል። ለነገሩ፥ እኛ አፍሪካውያን፥ የትም እንኑር የት፥ በአኅጉራችንም ሆነ በሌላው ዓለም፥ ላባችንን አንጠፍጥፈን ሰርተን፥ ተበድረንም ይሁን ተለቅተን ባገኘነው ገንዘብ መዝናናት የምንሻው ባብዛኛው በእነዚህ ሶስት ነገሮች ነው። ይሄም ሰፊ ርእስ ነው። ለጊዜው፥ ተማርን ከምንባለው መሀከል ጥቂት የማንባለው ከንባብ ይልቅ በእነዚህ ሶስት ነገሮች መዝናናትን የመረጥን እንደሚመስለኝ እመግለፅ ላይ እና፤ ብዙ ገንዘብ ሲኖረን ደግሞ ለንባብ የማንደራጀው ሰዎች ለእነርሱ ሲሆን ግን የምንደራጅ እንደሚመስለኝ እመጠቆም ላይ ላተኩር። ጉዳዩ ሁላችንንም እንደሚያሳስብ፥ እያሳሰበም እንደሆነ ከልብ አምናለሁ። ዛሬ በዚህ መንገድ በሩጫ የማነሳው ግን ተግባራዊ መፍትሔ ሳንሰጠው ስለቀጠልንበት ሁላችንንም ለመተንኮስ ነው።

በእየሰፈሩ ኢንፎርማል የሆኑ ማኅበሮች የተቋቋሙ ይመስላል። ወይ በሳምንት፥ ወይ በ15 ቀን፥ ወይ በወር የሚገናኙ "የመዝናኛ ፅዋዎች (ማኅበሮች)" ያሉ ይመስለኛል። ማኅበሮቹ እናቶቻችን የሚጠጡትን የፅዋ ማኅበር ይመስላሉ። ስለዚህም፥ እነሱም ፀበል ፃዲቅ አላቸው። ብዙ ጊዜ ጠዲቃቸው ጥሬ ስጋ (የፍየል፥ የጥጃ፥ የበግ፥ የላም፥ የበሬ) ይመስለኛል። ፀበላቸውም ዊስኪ፥ ኩርቫይዜር፥ ቪኖ፥ ጠጅ፥ ጂን ወዘተ ይመስለኛል። እርግጥ ምርጫቸው እንደየአቅማቸውና እንደየጣእማቸው ይለያያል። ማሳረጊያውም ብዙ ጊዜ ወሲብ ነው። የዘመኑ አስፈሪ ሁኔታ እማሳረጊያው ላይ መጠነኛ ለውጥ ሳያስከትል አልቀረም የሚል ግምት (ወይስ ምኞት?) አለኝ። በተረፈ ማኅበርተኞች በየሉካንዳው፥ በየታዋቂ ምግብ ቤቱ፥ በየመኖርያ ቤቱ እየተገናኙ ጠበል ጠዲቅ ይካፈላሉ[6]። እነዚህን በልክ ማድረግ በጣም ጤነኛ አኗኗር ብቻ ሳይሆን፥ ለአጠቃላዩ ማኅበራዊ ኑሯችን ሰላማዊና የተረጋጋ መሆንና ለስራም ቅልጥፍና የሚያደርገው አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አልጠራጠርም። ሲበዛና ሲንዛዛ ግን ሊያሳስበን ይገባል። ስጋዊ ስሜትንና ፍላጎትን እማርካት ላይ ስንተጋ፥ ሳናውቀው እነዚህን ስሜቶችና ፍላጎቶች በእየውስጣችን በትጋት እናረባለን፥ እናሳድጋለን፥ እናፋፋለን። ቀስ በቀስ የእነዚህ ስጋዊ ፍላጎቶች ተገዢ እንሆናለን። አእምሮን፥ ረቂቁን ስሜት ማለትም መንፈስንና ነፍስን ማዳበር፥ ማበልፀግ፥ መግራት ይቀራል። ስለዚህ ስለንባብ ልምድ ስንወያይ እንዲህ ዓይነቶቹን ቁምነገሮች እያነሳን ተምር እያሰብንባቸው ቢሆን መልካም ይመስለኛል።

---

[6] በነገራችን ላይ እነዚህ ማኅበራት ሶስት ዓይነት አደረጃጀት ያላቸው ይመስላል። ወንዶች ብቻ ያሉበት፥ ሴቶች ብቻ ያሉበትና ሁለቱም ፆታዎች ያሉበት። ይሄም ዝርዝሩ ሰፋ ያለ ነው።

## 5. የፈረንጅ ትምህርት ቤቶች

በኢትዮጵያ የወረዳ፥ የአውራጃ እና የክፍለሀገር ትምህርት ቤቶች ውስጥ የንባብ እድልና ልምድ እኩል፥ በእቅድ ተስፋፍቷል ወይም አልተስፋፋም ለማለት የሚያበቃ መረጃ መኖሩን አላውቅም፡፡ አለ ብዬ ግን አላስብም፡፡ በእኔ ግምት በስርዓትና በእቅድ የተኪያሄደ ነገር ቢኖር እጅግ ውሱን ይመስለኛል፡፡ በየትምህርት ቤቱ፥ በተለይ በመምህራንና በትምህርት ቤት ዳይሬክተሮች፥ አልፎ አልፎም በተማሪዎች ትጋት ስነፅሁፍና ንባብ የተበረታቱበት ሁኔታ ግን የነበረ ይመስለኛል፡፡ ይህ ሁኔታ ዛሬም አልፎ አልፎ ያለ ይመስላል፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን እነዚህ ተባህር ላይ ጠብታ የሚያልፉ አይደሉም፡፡

በአዲስ አበባ ከነበሩት ትምህርት ቤቶች፡- ተፈሪ መኮንን፥ ዊንጌት፥ ኮከበ ፅባህ፥ ዳግማዊ ምኒልክ ወዘተ.፣ ከክፍለሀገሮቹ ደግሞ የሐረር የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም የንባብ ነገር ሲነሳ ስማቸው በበጎ ከሚነሱት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነርሱም ቢሆኑ ከእነርሱ በኋላ ከመጡት የትምህርት ስርዓቶችና ሂደቶች ጋር ሲነፃፀሩ የሚያስደምሙ ይሆኑ እንደሆነ ነው እንጂ በብሔራዊ ደረጃ ስለነበረው የንባብ ልምድ ብዙ ይናገራሉ ለማለት የሚያስደፍር አይመስለኝም፡፡

እኔ የተፈሪ መኮንንን ተማሪ ነበርኩ፡፡ የራሴን ልምድ ከእናንተ ጋር ብጋራ ጠቃሚ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ በሀገራችን ስለነበረውና ስላለው የንባብ ባህል የተኪያሄደ ሳይንሳዊ ምርምር እስካሁን ስለሌለ፥ ስለንባብ ሊነገሩ የሚችሉትን የየግል ልምድ ተረኮችን (personal narratives) ማሰባሰብ በተለይ ስላለፈው ዘመን አንዳንድ መረጃ ለማቆየት ይረዳ ይሆናል ብዬ ነው "ጠቃሚ የሚሆን ይመስለኛል" ያልኩት፡፡ የእኔ ልምድ ባጭሩ እንዲህ ነበር፡፡

(1ኛ) የሂሳብ፥ የታሪክ፥ የጂኦግራፊ፥ የባዮሎጂ መፅሀፍ ከማንበብ የሚገኝ የንባብ ልምድ ነበረ፡፡ ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ብዙውን ትምህርት የተማርነው ጥቁር ሰሌዳ ላይ ኖት እየተገፈልን ሳይሆን መምህሩ "ሌክቸር ሲያደርግ" (ወይም እክፍል ውስጥ በቃሉ ሲያስተምር) የራሳችንን ማስታወሻ (note) እየወሰድን ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ወደ አስርና አስራ አንደኛ ስንሸጋገር ደግሞ ሙሉ በሙሉ በሌክቸር ነበር የተማርነው፡፡ ታድያ ለእያንዳንዱ ትምህርት አንዳንድ የመማሪያ መፅሀፍ ነበረ፡፡ ለእኛም አንዳንድ ይሰጠን ነበር፡፡ በጥናት ፕሮግራም እና እቤታችን በየቀኑ እንድናደርግ የሚጠበቀው፥

የወሰድነውን የሌክቸር ማስታወሻ የመማሪያ መፅሀፎቹን እያነበብን እንድናዳብር ነበር። ብዙ መምህራን፥ ይህንን መፈፀማችንን በማግስቱ ደብተራችንን እየተመለከቱ ይቆጣጠሩ ነበር። ይህ ስርዓት ብዙም አልቀጠለም።

ከዘመነ-ደርግ ጀምሮ፥ እንኳን በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ብዙ ተማሪዎች የሚያወሩት ስለ መፃህፍት ሳይሆን ስለ "ሺት" እና ስለ ተጣራች፥ ወይ የምትሸመደድ፥ ወይ በአጤሬራ ተፅፋ እፈተና ክፍል ስለምትወሰድ "ኖት" ነው። ስለዚህ የሁለቱ መንግስታት የትምህርት ስርዓቶች ካፈሯቸው ብዙዎቹ የ"አጥቂር" እንጂ የ"አንባብ" እና የ"ፃፍ" ትውልዶች አይደሉም ማለት ይቻላል። የፈጠራቸው ደግሞ፥ ትምህርትንና ፖለቲካን ሆነ ብሎ ያቀላቀለ፥ ክድርናን በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ስራዬ ብሎ የነዛ፥ ሙሉ ዓይኑን እና አእምሮውን እስልጣንና እጥቅም ላይ ያደረገ ፖሊሲና ተግባር ይመስለኛል። በዘመነ ደርግና በዘመነ ኢሕአዴግ ካድሬዎች፥ አድኃሪ ነው እየተባለ፥ ባንድ አፍ እስከዛሬ የሚዘለፈው የአፄ ኃይለስላሴ የትምህርት ስርዓት ያፈራቸው ሰዎች፦ (ሀ) ሀገሪቱ ውስጥ የነበረውን የአገዛዝ ስርዓት ለመተቸትና በተለያየ መንገድ ለመታገል፤ (ለ) በመንግስትና በግል ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ እውቀት በሚጠይቁ ሙያዎች ላይ ተሰማርተው ራሳቸውንና መንግስታቸውን ለማገልገል ችለዋል። (ሐ) በሀገሪቱ ውስጥ እና ከሀገሪቱ ውጭ ባሉ ኢንተርናሽናል ድርጅቶች፥ የምርምር ማእከሎች፥ ዩኒቨርሲቲዎች፥ ኮሌጆች፥ ኩባንያዎች ወዘተ. ውስጥ እንደሚሰሩ ነው የሚነገረው፥ የሚታወቀውም። የደርግና የኢህአዴግ ዘመኖች የትምህርት ቤቶች ውጤቶች ግን በወጣት ስደት እና ፍልሰት ነው የሚታወቁት። የሚሰደዱትም ከዚህ በፊት የነበረው ትውልድ ተሰማርቶባቸዋል የማይባሉትን ልዩ ልዩ የጉልበት ስራዎችን ሰርቶ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ለመርዳት ነው። እዚህ ጋ፥ ነጥቡ "ለምን የጉልበት ስራ ሰሩ?" የሚል አይደለም። እንዲያውም የጉልበት ስራ ይበልጥ እንስራ፥ በብዛት እንልመድ ከሚሉት ወገን ነኝ። ነጥቡ ግን ይሄ አይደለም። ታድያ ነጥቡ ምንድነው? ነጥቡ፥ በዓለም ገበያ ከፍተኛ ሙያን፥ ከፍተኛ እውቀትን ከመሸጥ ይልቅ ባብዛኛው ተራ፥ "ኔቸራዊ" ("ተፈጥሯዊ")፥ በወጉ ያልሰለጠነ ጉልበትን ወደመሸጥ መሸጋገራችንን ማመልከት ነው። የተሸጋገርንበት ዋና ምክንያት ደግሞ፥ የትምህርት ደረጃና ጥራት ከጊዜ ወደጊዜ ዝቅ እያለ ስለመጣ ነው የሚለውን ነጥብ ለመጠቆም ነው። ይህንን ከንባብ ጋር ስናያይዘው ደግሞ፥ የትምህርቱ ደረጃ ዝቅ እያለ በሄደ ቁጥር ተማሪው የሚያነብበት አጋጣሚ እያነሰ፥ እንኳን የስነፅሁፍ፥ የታሪክ፥ የፍልስፍና፥ የስነልቡና፥ የፖለቲካ፥ የሕይወት ታሪክ ወዘተ. መፃህፍትን ሊያነብ የትምህርት መፃህፍትንም የሚያነብበት ሁኔታ እጅግ ቀንሷል ያሰኛል።

## ቁዘማ፦ የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ

በዩኒቨርሲቲ ደግሞ ለአንድ ኮርስ የተመደቡ መፃህፍትንና ጆርናሎችን ፈልጎ ለማንበብ የሚጥሩ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ውሱን ይመስለኛል፡፡ እንዲያውም የትምህርቱ አኪያሄድ የይዘት ትምህርቶች መፃህፍትን በወጉ እንዲያነቡ፥ እንዲያጠኑና እንዲፅፉ ስለማያደርግም ነው ጥራቱ ዝቅ እንዲል የሚገደደው፡፡ የባዮሎጂ መማሪያ መፅሀፍ አንብቦ፥ የመምህሩን የክፍል ውስጥ "ሌክቸር" ማስታወሻውን እመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ካለው መረጃ ጋር እያስተያየ አዳብሮ፥ እደብተሩ ውስጥ የተሟላ ማስታወሻ (note) እየፃፈ ካልተማረ፤ መረጃ መሰብሰብ፥ የመረጃዎችን ዋጋ እየመዘኑ መለየት፥ መረጃዎችን ማደራጀትና በመልክ በመልኩ መከልሰፍ፥ መረጃዎችን ማነፃፀር (compare ማድረግ)፥ መረጃዎችን ማለፃፀር (contrast ማድረግ)፥ መረጃዎችን ማጣጣምና መተንተን ካልተማረ ተምሯል ማለት ያስቸግራል፡፡

እርግጥ የይዘት ትምህርት መፃህፍትን በዚህ መንገድ እየመረመሩ የተማሩት ሁሉ አንባቢ አልሆኑም፡፡ ነገር ግን፥ የአፄው ዘመን የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከደርግና ከኢህአዴግ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተሻለ የማንበብ እድል ይሰጡ ነበር ማለት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ለዚህም አንዳንድ መረጃ በሩጫ መጥቀስ ቀላል ይመስለኛል፡፡

(2ኛ) ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ በምንማራቸው የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርቶች ውስጥ በየደረጃው የስነፅሁፍ ስራዎች ይገቡ ነበር፡፡ በተጨማሪም ከቤተመፃህፍት መፃህፍት እያወጣን የምናነብበት ስርዓት ነበር፡፡ ከ7ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ስንማር በየክፍላችን የተመረጠ ቤተመፃህፍተኛ (librarian) ነበረን፡፡ ከትምህርት ቤቱ ቤተመፃህፍት የምንዋሰውን በየሳምንቱ እክፍላችን ድረስ እርሱ ያመጣልን ነበር፡፡ ባለፈው ሳምንት ተውሰን የነበረውን ደግሞ ወደ መፃህፍት ቤቱ ይመልስልናል፡፡ በዚህ መንገድ መፅሀፍ የማንበብ ልምዳችንን እንድናዳብር ይደረግ ነበር፡፡ አንዳንዶቻችን ተጨማሪ ዘዴዎች ነበሩን፡፡ ለምሳሌ፥ እኔና ሁለት ሌሎች ጓደኞቼ ለሳምንቱ የተዋስነውን የየራሳችንን መፅሀፍ ቶሎ አንብበን ጨርሰን እርስ በርስ የምንለዋወጥበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት፥ በሳምንት የምናነበውን መፅሀፍ ቁጥር ብዙ ጊዜ ሁለት አንዳንዴም ሶስት እናደርስ ነበር፡፡ በመሀከላችን "የእኔ እበልጥ! እኔ እበልጥ!" መልካም ፉክክር ነበር፡፡ ሌላው ጠቃሚ ምሳሌ በዚሁ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ አማርኛ ቋንቋ እማር የነበረበት ሁኔታ ነው፡፡ <u>**አርአያ**</u>ና <u>**ራሴላስ**</u> በተባሉ ልቦለዶች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ እንደተማርኩ አስታውሳለሁ፡፡ ለትምህርቱ ሲባል የመፃህፍቱ አንዳንድ ቅጂዎች ከትምህርት ቤቱ የመፃህፍት ግምጃ ቤት ተሰጥተውኝ የነበር ይመስለኛል፡፡ ዛሬ፥ ተማሪው ትምህርት ቤት ከገባበት ጊዜ ጀምሮ 12ኛ ክፍል

ጨርሶ እስኪወጣ፥ ከትምህርት ቤቱ የመፃህፍት ግምጃ ቤት ለትምህርት ተብሎ የሚሰጠው አንድ ልቦለድ አለ ብዬ አልገምትም። ይህ አስተያየት ትክክል ከሆነ ስለዚህ ዓይነቱ ተማሪ የንባብ ልምድ እንዴት መነጋገር ይቻላል? እድለኛ ሆኖ፥ በግሉ፥ በቤተሰብና በወዳጅ ዘመድ ተፅእኖ ተገፋፍቶ፤ የትምህርቱን ስርዓት የፀረ-ንባብ መንፈስ ተቋቁሞ፥ ልምዱን በግሉ ካላደበረ በቀር ከየት ያመጣዋል? በዚህስ ማነው ተወቃሹ?

ሌላ አንድ ምሳሌ ልጨምር። አንዳንዴ የታዋቂ ሰውን ስም እየጠሩ ምሳሌ መስጠት ረቂቁን (abstract የሆነን ነጥብ) አግዝፎ ለማሳየት ስለሚረዳ የመጨረሻውን ምሳሌዬን ጠቅላይ ሚንስትር መለስን ላድርግ። አቶ መለስ በትግርኛ፥ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው ይታወቃሉ። ለጊዜው ስለእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው ምሳሌ አድርገናቸው እንነጋገር። ይህንን ችሎታቸውን ከየት አመጡት? በእኔ አስተያየት ከየትም አላመጡት። ያገኙት፥ ከሁሉ አስቀድሞ ከአፄ ኃይለስላሴ የትምህርት ስርዓት እና ከግል ጥረታቸው ይመስለኛል። ከትምህርት ቤት በኋላም በተለይ በንባብ አዳብረውታል ብዬ አስባለሁ። ይሁን እንጂ እድቡሽት ላይ በተሰራ ቤት ላይ መገንባት እንደሚያስቸግር ሁሉ፥ እርሳቸውም መሰረታቸው በወጉ የተሰራ ባይሆን ክሂላቸውን ማዳበር ያዳግታቸው ነበር። ታድያ፥ እርሳቸው በእንግሊዝኛ አፄ ኃይለስላሴን የበለጡ-የበለጡ ይመስለኛል። አፄ ኃይለስላሴ፥ ምናልባት እራሳቸው በወጉ የማያውቁትን ቋንቋ በእርሳቸው ዘመን በተከፈቱ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተማሩ ብዙ ተማሪዎች እንዲካኑት አድርገዋል። እርሳቸው ብዙ ስነፅሁፍ ባላነበቡበት ቋንቋ አቶ መለስ እና የተለያዩ የአፄው ዘመን ተማሪዎች እንዲያነቡ አድርገዋል።

አሁን አስፈሪው ጥያቄ ሊመጣ ነው። በአቶ መለስ ዘመን በመንግስት ትምህርት ቤቶች የተማሩ ተማሪዎች ሁኔታ ምን ይመስላል? ከእርሳቸው የሚበልጡ ተማሪዎች ቀርቶ እርሳቸው በእንግሊዝኛ ሲናገሩ ምን እንደሚሉ በትክክል የሚሰሙና የሚረዱ ተማሪዎች አፍርተዋል?[7] በቅርቡ አፈራለሁ የሚል የውነት ተስፋስ አላቸው? ተስፋው ካላቸው፥ መልካም። ተስፋው ከሌላቸው ግን፥ ቀላል ዲስኩር ሰምቶ መረዳት የማይችል ተማሪ የማንበብ ልምድን በምኑ ያዳብረዋል? እንግሊዝኛው እራሱ ከሌለው፥ በወጉ ካልተማረው በእንግሊዝኛ የማንበብን ባህል ከምኑ ያመጣዋል? አማርኛው እራሱ፥ ቋንቋው ከሌለው፥ በወጉ ካልተማረው በአማርኛ የማንበብን ባህል ከምኑ ያመጣዋል? የሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ስሞች በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቦታ እየተካን ጥያቄ መጠየቃችንን ስንቀጥል መክረም እንችላለን። የምናገኘው መልስ ግን ያው "ከየትም አያመጣው!" የሚል ነው።

---

[7] ከዘመነ ደርግ የወረሱትን የትምህርት ስርዓት አልዘነጋሁም። ያንንም ተግምት ውስጥ አስገብቼ ነው የሚከተሉትን ጥያቄዎች ገፍቼ የምጠይቀው።

ስለዚህ ያሁኑ የትምህርት ስርዓት፥ ለጊዜው አሁን በምንነጋገርበት ጉዳይ፥ ከአፄው ዘመን የትምህርት ስርዓት ጋር የሚወዳደርበት አቅም የለውም ማለት ይቻላል።

ከዚህ በላይ የይዘት ትምህርት መፃህፍትን አጥርተው እያነበቡና እየመረመሩ የተማሩት ሁሉ አንባቢ እንዳልሆኑ ገልጬ ነበር። ለምን እንዳልሆኑ ግን ፍንጭም ሳልሰጥ ነበር ያለፍኩት። አሁን አንዳንድ ነጥቦች ልጠቃቅስ።

የተለያዩ የስነፅሁፍ፥ የፍልስፍና፥ የታሪክ፥ የስነልቡና፥ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ ወዘተ. መፃህፍት የማንበብ ልምድ ከብዙ ሌሎች ጉዳዮች ጋርም ይያያዛል።

⇒ መጀመሪያ በሆነ ምክንያት የዳበረ (ለምሳሌ በቤተሰብ፥ በዘመድ፥ በጎረቤት፥ በመምህር፥ በትምህርቱ ስርዓት ወዘተ. ምክንያት) መፅሀፍ የማንበብ ፍላጎት መኖር አለበት። ይህ እጅግ መሰረታዊ መነሻ ነው። ስለዚህ፥ ዛሬ የምንወያየው "እርሱ እንዴት መኖር አለበት?" እያልን ቢሆን መልካም ይሆናል።

⇒ መፃህፍት የማንበብ ልምድና አዲስ ፍላጎት ሲኖር ደግሞ፥ ከዚህ በታች ስለተዘረዘሩት ጉዳዮችም ለማሰብ እንገደዳለን። ምክንያቱም፥ ልምዱ እና ፍላጎቱ ኖረውም ማንበብ የማይቻልባቸው፥ ስለዚህም ባንድ ሀገር ውስጥ የንባብ ባህል የማይዳብርባቸው ምክንያቶች አሉ። ጥቂቶቹን በሩጫ ልጠቃቅስ።

- አንባቢን የሚስቡ፥ ከሳቡ በኋላም ፍላጎቱን የሚያረኩ፥ የመፃህፍት ረሀቡን የሚጨምሩ፥ የአንብብ-አንብብ ስሜቱን የሚኮተኩቱ መፃህፍት በገበያው ላይ መኖር አለባቸው፤

- መፃህፍቱን መግዣ ገንዘብ፥ ወይም መፃህፍቱን ማግኛ ሌላ ዘዴ (ለምሳሌ ልዩ ልዩ መፃህፍት ቤት፥ የመፃህፍት እቁብ፥ የመፃህፍት ኪራይ፥ የመፃህፍት "ሳልቫጅ" ወዘተ.) እንደልብ መኖርና መስፋፋት አለበት፤

- የቦታ ጥያቄም አለ። ማንበብያ ቦታም ይቸግራል። ዛሬ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለውን የሰው ብዛትና የዚያን ቤት መጠን ወይም የክፍሎች ብዛት ስንመለከት ባብዛኛው ከነዋሪው ቁጥር ጋር አይመጣጠንም ብዬ አስባለሁ። ስለዚህ፥ ፓርኮችና ቤተመፃህፍት ባልተስፋፉበት ሀገር፥ "አንድ ሰው የት ቆሞ፥ የት ተቀምጦ መጽሐፍ ያንብብ?" ብሎ መጠየቅም ያስፈልጋል።

- በዚህ ላይ መብራት በሀገራችን እንደልብ አልተስፋፋም። የመብራት መስፋፋት ከመፅሀፍ የሕትመት፥ የስርጭት እና የንባብ ሁኔታ እና በጠቅላላው ከመፃህፍት ኢንዱስትሪና ንግድ ጋር ተገናኝቶ የሚጠና ቁምነገር ነው። የአንድ ሀገር ማኅበራዊ፥

ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የንባብን ባህል ለማፋፋት ወይም ለማጫጨት እንደሚችል ስለሚታወቅ በቴክኖሎጂና በኢኮኖሚ በለሙት ሀገሮች ያሉ የስነፅሁፍ የምር (serious) ሃያስያንና ተመራማሪዎች እነዚህን ጉዳዮች አበጥረው በማጥናት ይካናሉ።

-ለምሳሌ፥ የራሱን የእንግሊዝኛን ልቦለድ (the English novel)ታሪክ ያጠኑ ታዋቂ ምሁራን የልቦለድ ዘውግ በሀገሪቱ ያደገው የኢንዱስትሪ አብዮት ያመጣቸው የአኗኗር ዘይቤዎችና የኤሌክትሪክ ብርሃን መስፋፋት ባደረጉት አስተዋፅኦ ጭምር መሆኑን በዝርዝር ፅፈዋል፤

-በእኛም ሀገር፥ በዘመነ ደርግ በኤርትራና በትግራይ (በተለይ ግን በኤርትራ) ተሰማርቶ የነበረው የኢትዮጵያ ወታደር ለካሴት ዘፈኖችና ለአማርኛ ልቦለዶች ልዩ ገበያ ከፍቶ እንደነበር የገበያው ተጠቃሚዎች እና አንዳንድ ታዛቢዎች ይናገሩ ነበር። ለምሳሌ፥ አቶ ብርሃኑ ዘሪሁን እና አቶ ደበበ ሰይፉ ሁኔታውን በአዎንታዊ መልኩ ሲጠቅሱ፥ አቶ መንግስቱ ደግሞ ጥቂት ምፀት ቀልቀል አድርገውበት ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ሌሎች በህይወት ያሉ ሰዎችም የአቶ ብርሃኑን እና የአቶ ደበበን ሃሳብ ሲጋሩ በተለያዩ ሁኔታዎች ሰምቻለሁ[8]። ታድያ፥ ይህ ጉዳይ እኔ እስከማውቀው ድረስ ገና በወጉ ስላልተጠና፥ እስኪጠናና እውነቱ እስኪታወቅ፥ ያው በ"ተብሏል!" እና በ "አሉ!" ይቆያል።

-የእኛን ሀገር የመብራት ሁኔታ በሚመለከት ደግሞ ሁላችንም የምናውቃቸውን አንዳንድ ነጥቦች እያነሳን እናስብ። ቀን-ቀን በስራ ላይ የሚውሉ፥ ማታ-ማታ ወይም ሌሊት-ሌሊት ማንበብ ቢፈልጉ ልዩ ልዩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፦ (1) እሚኖሩበት ቤት መብራት ጨርሶ ከሌለ የሚያጋጥማቸው መሰረታዊ ችግር የታወቀ ነው፤ (2) መብራት ኖሯቸው፥ ቤቱ የኪራይ ቤት ከሆነ ደግሞ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፤ (3) ቤቱና የመብራት ቆጣሪው የራሳቸው ሲሆኑ ደግሞ የመብራት ዋጋ ውድነት ብዙው ሰው ችላ ሊለው የማይችል ጫና አለው።

እንግዲህ፥ አራምባና ቆቦ እያልኩም ቢሆን አንዳንድ ነጥቦችን አንስቻለሁ። ሃሳቦቹን ብቻ ሜዳ ላይ ዘርቼ ከምሄድ ካንዳንድ ተግባራት ጋር በሩጫም ቢሆን ላያይዛቸው ልሞክር።

## 6. ምን ይደረግ?

---

[8] በሚያዝያ 15/1997 "የንባብ ክለብ" (Reading Club) ፓናል ላይ አቶ ሣህለስላሴ ብርሃነማርያም፥ አቶ አስፋው ዳምጤ እና ስማቸውን የማላውቃቸው ሁለት ሰዎች ስለጦሩ (በተለይ ሰለወጣት የጦር አባላት) አንባቢነት ተናግረዋል።

⇒ በመጀመሪያ፥ ደግመን ደጋግመን መወያየት አለብን። መነጋገር ያለብን "መፅሀፍ የማንበብ ልምድ በኢትዮጵያ ለምን አልዳበረም?" ብለን በየፊናችን ጠይቀን በዚያ ላይ መሆን ይኖርበታል። ጥያቄዎቹ በሙሉ በአደባባይ እንዲታወቁ፥ እንዲህ እንደዛሬው የየራሳችንን ቁዘማ የምር ማኪያሄድ፥ በዚያ ላይ ደጋግሞ መወያየት እና በሰፊው መነጋገር ይጠቅማል። በመገናኛ ብዙኃን፥ በትምህርት ቤቶች፥ በተለያዩ አጋጣሚዎች ስንገናኝ ሀሳባችንን ሳንቆጥብ መለዋወጥ፥ ማጋራትና መጋራት አለብን። ይህንን ማድረግ ብዙዎቻችንን ያነቃል፤ ሃሳቡም ይብላላል፥ ይስፋፋልም። ውይይቱን፥ በየከተማው ያሉ ልዩ ልዩ የድርሰት ማኅበራትም በተደራጀ መልክ ሊያኪያሄዱ ይችላሉ። በተጨማሪም፥ በቅርቡ እንደገና የተቋቋመው "የኢትዮጵያ የደራስያን ማኅበር" እና "መፃህፍት ለኢትዮጵያ" የተባለው ይህ የንባብ ማኅበር በዚህ ጉዳይ የተለየ ትብብር እንዲያደርጉ፥ ልዩ ልዩ ውይይቶችን በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ያለማሰለስ እንዲያኪያሄዱ መምከር እወዳለሁ። እነዚህ ሁለት ማኅበሮች በሀገሪቱ ውስጥ እስከዛሬ የተቋቋሙትን የስነፅሁፍና የንባብ ክበቦች ዝርዝር፥ አድራሻ፥ የመተዳደሪያ ደንብ እና ማኅበራቱ እስከዛሬ ያከናወኗቸውን ተግባራት የሚገልፅ አንድ ሰነድ ቢያዘጋጁ ስራቸውን በእቅድ፥ በእውቀት፥ በስርዓት እና በቅልጥፍና ለማኪያሄድ ይችላሉ ብዬ ስለማምን ይህንን ሰነድ እንዲያዘጋጁም አጥብቄ እመክራለሁ። ይሁን እንጂ ይህ ብቻ አይበቃም።

⇒ ሰፋና ጠለቅ ያለ ጥናትም ማድረግ ይኖርብናል። ጥናቱም ለጥናትነቱ ሲባል ብቻ፤ አኃዞች፥ ግራፎችና ሰንጠረዦች ለመደርደር ብቻ የሚከናወን መሆን የለበትም። ባህሉ ለንባብ እና ለአንባቢ የሚሰጠው ቦታ ምን እንደሆነ ፍርጥርጥ አድርጎ የሚመረምር መሆን ይጠበቅበታል። ከዚያ በሀገሪቱ የቄስና የፈረንጅ ትምህርት ቤቶች ለንባብ እና ለአንባቢ የሚሰጠውን ቦታ ማጥናት አለብን። እየተራቀቀ የመጣው የዲጅታል፥ የኢንተርኔትና እና የሳተላይት ቴክኖሎጂ በጥቅሉ፥ በሰዎች የመዝናኛ፥ የእውቀት ማሰራጫና መለዋወጫ መንገዶች ላይ ያመጣቸውን መሰረታዊ ለውጦችም መመልከት ይኖርብናል።

⇒ ከዚያ መሰረታዊና ከተግባር ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን እያነሳን መወያየትና ወደተግባር ማምራት አለብን ብዬ አስባለሁ። አንዳንዶቹን ጥያቄዎችና አስተያየቶች ከእናንተ ጋር ተጋርቼ ላብቃ፦

## ቁዘማ፦ የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ

- **በዝቅተኛና በከፍተኛ ደረጃ ተምረናል የምንባል ሰዎች፥ እያንዳንዳችን በየራሳችን ምን እናድርግ?** በቡድን ወይም በማኅበር ሆነን ምን እናድርግ? ለምሳሌ፥ ከነገ ጀምሮ የጎረቤት ወይም የጓደኞች ወይም የቤተሰብ የንባብ ማኅበር ማቋቋም አንችልም? ሁለት ሆነን መጀመር እንችላለን። እንዲህ ዓይነቱን ማኅበር ማቋቋምን በተግባር መሞከርና እንዲህ እንደዛሬው በትውር ማቀድ አንድ አይደለም። ተግባር ይዞ የሚመጣቸው ብዙ የራሱ ልምዶች አሉ። ስለዚህ በያለንበት በተግባር ለማቋቋም እንጀምርና የዛሬ ሶስት ወይም ስድስት ወር ስንገናኝ ስለ ተግባር-ነክ ልምዳችን እንወያይ። በየፊናችን ለማቋቋም ከሞከርን በኋላ የምናደርገው ውይይት እጅግ የተለየና የንባብ ልምድን በኢትዮጵያ የምናዳብርበትን ተግባራዊ መንገድም ከዛሬው በበለጠ ደረጃ እንደሚያመለክተን ጥርጥር የለኝም።
- **በየቤቱና በየጎረቤቱ ምን እናድርግ?** በጎረቤት ጠላ ቤቶች፥ ጠጅ ቤቶች፥ አረቂ ቤቶች ማንበብ የሚቻልባቸው መንገዶች በየአካባቢው መፈለግ የሚቻል ብቻ ሳይሆን ቀላል ይመስለኛል። በየአካባቢው ተሰሚነት ያላቸውን ሰዎች ይዞ፥ የየአካባቢውን አኗኗርና ፍላጎት እያጠኑ ንባብ ሊኪያሄድባቸው የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይቻላል። በእንዲህ ዓይነት መድረኮች፥ ነዋሪዎች የየአካባቢያቸውን የኑሮ ሁኔታ እያነሱ በነፃ ሊወያዩ ይችላሉ።
- **ትምህርት ቤቶች ምን ያድርጉ?** በትምህርት ቤቶች ያሉ የስነፅሁፍ ክበቦች ይበልጥ እንዲዳብሩ፥ አዳዲሶችም እንዲመሰረቱ በየትምህርት ቤቱ ስለንባብና ስነፅሁፍ ልዩ ልዩ ውይይቶችና ክርክሮች ማኪያሄድ ያስፈልጋል።

ትምህርት ቤቶች ሰላማዊ የውትወታ ስራ (የ lobby ስራ) መስራት መለማመድ አለባቸው። ለምሳሌ፥ እንደ "**ጦብያ፥ ወዳጄ ልቤ፥ አርአያ፥ እንደወጣች ቀረች፥ አርአያ፥ ራሔላስ፥ መስከረም፥ ፍቅር እስከ መቃብር፥ የቴዎድሮስ እንባ፥ ያዲስ አባ ተረቶች፥ አደፍርስ፥ ካድማስ ባሻገር፥ የጎሊና ደወል፥** ወዘተ." የመሳሰሉት የአማርኛ ልቦለዶች ታትመው፥ የታተሙበትን ዋጋቸውን ሊሸፍን በሚችል ዋጋ ብቻ፥ በሌላ አነጋገር በርካሽ፥ በየትምህርት ቤቱ እንዲሸጡ መምህራንና ተማሪዎች ሊወተውቱ (lobby ሊያደርጉ) ይገባል ብዬ ተምር አስባለሁ። በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና በእንግሊዝኛ ለተፃፉ መፃህፍትም እንዲሁ የውትወታ ስራ መስራት ይገባል።

## ቁዘማ፡- የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ

በየትምህርት ቤቱ በተለይ ከቋንቋና ከስነምግባር ትምህርቶች ጋር የተያያዙ መፃህፍት፥ በመፃህፍት ግምጃ ቤቶች በኩል እየተገዙ በርካሽ እንዲሸጡ፥ በትምህርቶቹ የንባብ ዝርዝር ውስጥ (required reading list) ውስጥ እንዲገቡም በሰለጠነና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መወትወት አለባቸው፡፡

- **የብዙኃን መገናኛዎች ምን ያድርጉ?**

ሬድዮ ምን ያድርግ? ቴሌቪዥን ምን ያድርግ? ጋዜጦችና መፅሄቶች ምን ያድርጉ? በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የምንሰራ ሰዎችስ ከነገ ጀምሮ ምን እናድርግ?

ስለነዚህ ጥያቄዎች ሁላችንም አስበን ከነገ ጀምሮ አንዳንድ እርምጃዎችን በቀላሉ ልንወስድ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፥ በተለይ የግል ጋዜጦች ያላቸው፥ በየጋዜጣቸው የአዳዲስ መፃህፍትን ታትሞ መውጣት በነፃ ማስተዋወቅ፤ በየጋዜጣችው "ከመፃህፍት አምባ" የሚል አምድ ከፍቶ የጥንቶቹንና የዛሬዎቹን መፃህፍት ከአንባብያን ጋር ማስተዋወቅ ይችላሉ፡፡ ይህንን በማድረግ ለስነፅሁፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ እስከዛሬ ጋዜጦቻቸውን ገዝተው የማያነቡ አዲስ አንባቢዎችም ሊያፈሩ ይችላሉ፡፡ የግል ጋዜጦች፥ ለሀገር ልማት የራሳቸውን አስተማማኝና ተግባራዊ አስተዋፅኦ እውን የሚያደርጉበት አንዱ እድላቸው ይህ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ፥ ይህንን ከማድረግ የሚቆጥባቸው ነገር ሊኖር የሚገባ አይመስለኝም፡፡

- **ኢትዮጵያውያን ሀብታም ግለሰቦች ምን እንዲያደርጉ እናሳስባቸው፥ እንጎትጉታቸው?** በእኔ አስተያየት ብንቀርባቸው፥ አንዳንድ የንባብ ፕሮግራሞች ላይ እየተገኙ እንዲያዳምጡ ከገፋፋናቸው ቀስ በቀስ የሚተባበሩበት ሁኔታ ይመጣል፡፡ የማያቋርጥ፥ የማይሰለች ውትወታ (lobbying) ግን ያስፈልጋል፡፡ አንዴ ጠይቆ፥ ባንድ ጊዜ የሚገኝ ምንም ነገር የለም፡፡ ዛሬ የእናት ጡትም ሆነ እንጀራ በቀላሉ የሚገኝበት ጊዜ አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይ ብዙ ማስረዳት፥ ብዙ ማስታወስ፥ እና አንዳንዴም በስልት ማባበል ያስፈልጋል፡፡ መቼም ስራ መስጠት ቀላል ስለሆነ ለኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር አንድ ትልቅ ስራ ልስጥ፡፡ ስነፅሁፍ ከሚስፋፋና ከሚዳብርባቸው መንገዶች አንዱ የስነፅሁፍ ሂስ ነው፡፡ ማኅበሩ የተለያዩ ምንጮችን አቀናጅቶ በሶስት ወር አንዴ የሚታተም የስነፅሁፍ ሂስ ብቻ ማተም የሆነ ጋዜጣ ወይም መፅሄት እንዲያቋቁም አጥብቄ አሳስባለሁ፡፡ ይህ እውን እንዲሆን እኔም የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡

- **የሲቪክ ማኅበራትስ? ከነገ ጀምሮ በያካባቢያችን ምን እንዲያደርጉ እንወትውታቸው?** እኛስ ከእነሱ ጋር ሆነን ምን እናድርግ?

**ቁዘማ፡- የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ**

የሲቪክ ማኅበራት ብዙ ጊዜ የሚያተኩሩት ከዲሞክራሲ፥ ከስርዓተ ፆታ፥ ከድኅነት፥ ከ"ጎጂ ባህል"፥ ከኤንቫይረንመንት ወዘተ. ጋር በተያያዙ ርእሰነገሮች ላይ ነው። እነዚህ ርእሰነገሮች፥ በተለይ ፊደል ወዳልቆጠረው አብዛኛው የሀገሪቱ ህዝብ ዘንድ ለማድረስ የሚፈልጓቸውን ቁምነገሮች፣ በምርምር፥ በልምድና በጥበብ ላይ ተመስርተው በሚዘጋጁ አጫጭር ትረካዎች፥ አጫጭር ትያትሮች፥ አጫጭር ጭውውቶች፥ ግጥሞች፥ ቀልዶች ወዘተ. እያዋዙ ማድረስ ይቻላል። በዚህ ረገድ እስከ ዛሬ የተደረጉ ሙከራዎች አልፎ አልፎ ይታያሉ። ጥቂት የማይባሉት በእውቀትና በጥበብ የተከሸኑ አይደሉም። ከተራ የቡና ቤት (ጥቂት የማይባሉት የሚኪያሄዱትም በመጠጥና ቡናቤት መቸቶች ነው) ወሬ የማያልፉ ነገሮች በትያትርና ጭውውት ስም በሬድዮና በቴሌቪዥን ሲተላለፉ አጋጥመውኛል። መቼም መልካካም ስራዎች መኖራቸው አይቀርም። ዋናው ቁምነገር ስነፅሁፍ ለልማት ሊያደርግ የሚችለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ሆኖ ሳለ እስከ ዛሬ በዚህ መስክ የተከናወነው ጥቂት መስሎ ይሰማኛል። ምናልባት የነቁት ደራስያንና የነቁት የሲቪክ ማኅበራት ሰዎች ስላልተገናኙ ይሆናል ይህ የሆነው። ወደፊት በዚህ መስክ ብዙ እንቅስቃሴ ማድረግ ይቻላል፥ ይገባልም።

- **የኢትዮጵያ መንግስት ምን እንዲያደርግ እናሳስበው፥ እንጎትጉተው?** የትም ሀገር፥ መንግስታት ጥያቄ ተጠይቀው ወዲያው መልስ፥ በተለይ ደግሞ የእውነት መልስ አይሰጡም። ብዙ ጥያቄዎች ስለሚቀርቡላቸው፥ እነርሱም የየራሳቸው ጥያቄዎችና ዓላማዎች ስላሏቸው ቶሎ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ቁጥር እጅግ ውሱን ነው። በተለይ በእንደኛ ያሉ ሀገሮች ውስጥ ያለው የአስተዳደር መዋቅር በሕግና በደንብ ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚሰራበትን ስርዓት ገና ስላላለማ ብዙ ክትትል፥ ማስታወስ፥ ፊት ማስመታት እና ውትወታ ይፈልጋል። ታድያ ውትወታው በቢሮዎች ብቻ ሳይሆን በተገኘው መድረክ ሁሉ መሆን ይኖርበታል። በየስብሰባው ላይ፥ በየጋዜጣና መፅሔቱ ላይ፥ በየተገኘው የሬድዮና የቴሌቪዥን ኢንተርቪው ላይ ወዘተ. መወትወት ያስፈልጋል። "ይሄ የማን ሬድዮ ጣብያ ነው? የማን ቴሌቪዥን ጣቢያ ነው? የማን ጋዜጣ፥ የማን መፅሔት ነው?" ሳይሉ በተገኘው እድል ሁሉ የሚያምኑበትን ሃሳብ መዝራት ያስፈልጋል። አጥብቆ መወትወት ይገባል። ስለዚህ፥ ስነፅሁፍን፥ ፊልምን፥ ትያትርን፥ ቪድዮን፥ ካሴትን፥ በጥቅሉም ባህልን እና ኪነጥበብን በሚመለከት መንግስትን ያላንዳች ማሰለስ፥ በየተገኘው መድረክ መወትወት ያስፈልጋል።

**ቁዘማ፦ የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ**

በኢትዮጵያ ውስጥ የልማት ጉዳይ ሲነሳ መንግስታት፥ ሹሞቻቸው እና ፊደላውያን አማካሪዎቻቸው ብዙ ጊዜ የሚታሰባቸው ቁሳዊ ልማት ነው:: በአፋቸው የሚያወሩት ስለ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፥ ስለ መንገድ፥ ሆስፒታል፥ ፋብሪካ፥ ህንፃ፥ ትምህርት ቤት ወዘተ. መስራት ነው:: በልማት ውስጥ የኪነጥበብ እና የባህል ሚና ምን እንደሆነ ያን ያህል ቀርቶ እንዲያው የምር በሚባል ደረጃ እንኳን ሲያነሱት አይገኙም:: በሰሞኑ የምርጫ ክርክር ውስጥ እንኳ ኪነጥበብ እና ባህል "ይሄ ነው!" የሚባል ስፍራ አልተሰጣቸውም:: ነገር ግን የኢትዮጵያ የልማትና የፖለቲካ ችግር በመሰረቱ የባህል ችግር ነው:: ይህ አነጋገር ብዙ ፊደላውያንን እንደሚያስቅ ለአፍታም አልጠራጠርም:: ምክንያቱም ፍጥጥ ብሎ የሚታዩዋቸው ችግሮች እንጀራ፥ ዳቦ፥ ውኃ፥ ልብስ፥ መጠለያ፥ ህክምና ወዘተ. ስለሆኑ ነው:: ነገር ግን እነዚህን ማስወገድ የሚቻለው በስራ ነው:: ስራ ደግሞ ብድግ ብለን የምንገባበት እንቅስቃሴ አይደለም:: መጀመሪያ መወያየት፥ መመካከር፥ መግባባት፥ እቅድ ማውጣት ወዘተ. ያስፈልጋል:: እዚህ ጋ ነው የባህል ጥያቄ አፍጥጦ የሚመጣው:: ተማርን የምንባለው ፊደላውያን ባብዛኛው የምናውቀው፥ ትምህርት ብለው በተለይ እውጭ ሀገር ያስተማሩንን ነው:: ከእኛ ሀገር እውነታ የበቀሉ ትውሮችን ሳይሆን ከሰው ሀገር ታሪክና ልምድ ውስጥ የነጠሩ ትውሮችን ነው ባብዛኛው የምናውቀው:: አልሚዎች የምንባለው እኛ እናለማዋለን ከምንለው ገበሬ ጋር መግባባት አንችልም:: የምንለዋወጣቸው ቃላት አንድ ሆነው እንኳ መግባባት ያስቸግረናል:: አንድ ገበሬ ሃሳቡን ለአንዳችን ለመግለፅ የሚናገረው ለዘመናት የሚያውቀውን አካባቢያዊውን፥ በሀገሩ ውስጥ ሲነገር የሰማውንና ሲደረግ ያየውን እያሰላሰለ እና ከእነዚህ ልምዶች የወጡትን ትውፊታዊ (ሀገር-በቀል) ትውሮች በአእምሮው ይዞ ሲሆን፤ እኛ የምንሰማውና የምንደሰኩርለት ደግሞ የእንግሊዝን፥ የአሜሪካንን፥ የኖርዌይን፥ የፈረንሳይን ወዘተ ምሳሌዎች፥ ልምዶች እና በፅሁፍ የሰፈሩ ትውሮች በአእምሯችን እያሰላሰልንና እያሰብን ነው:: የምንለዋወጣቸው ቃላት ብዙ ጊዜ አንድ ስለሆኑ የተነጋገርን፥ የተወያየን፥ የተግባባን ይመስለናል:: እውነቱ ግን ከዚህ የራቀ ነው::

በእኔ አስተያየት፥ ማንኛውም የልማት እንቅስቃሴ ፍሬ ሊያፈራ የሚችለው በእውቀት ላይ ተመስርቶ፥ አልሚውን እና ለሚውን አውቆ፥ ሁለቱን አስተዋውቆ፥ ሃሳብ አለዋውጦ፥ መክሮና ተግባብቶ አብሮ መስራት ሲቻል ነው:: መተዋወቅ የሚቻለው ደግሞ የባህል ጥናትና ልውውጥ ሲኖር ነው:: ባህልን እራሱን ማልማት ሲቻልም ነው:: ስነፅሁፍ መፃፍና ማንበብ የባህል አካል ስለሆነ ቢያንስ ቢያንስ ከቁሳዊ ልማት እኩል መታየት አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ::

## ቁዘማ:- የንባብ ጉዳይ በኢትዮጵያ

ከዚህ በላይ የተነሱትን ጥያቄዎች በአጥጋቢ መልክ እዚህ፥ ዛሬ፥ በቀላሉና በጥድፊያ መመለስ አይቻልም፥ አይገባምም:: በነበረኝ ጊዜ፥ አንዳንዶቹን እያነሳሁ የራሴን አስተያየት አልፎ-አልፎ ለመሰንዘር ሞክሬያለሁ:: በተረፈ፥ እነርሱን እና ሌሎች ጥያቄዎችን በጥሞና ሰብስቦ፥ ነባር ሰነዶችን መርምሮ፥ በባለሙያዎች ተወጥኖ በሚደረግ ጥናት ለመመለስ መሞከር ግን ይቻላል:: ታድያ ባጓጉል መራቀቅ ጊዜ መፍጀት ግብዝነት መሆኑን መገንዘብና መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: "በእቅድና በእውቀት ይሰራ፥ ይወጠን" ማለት "በስርዓት እንስራ!" ማለት እንጂ "በሆነ ባልሆነው ሰበብ እንዘናጋ፥ እናዝግም!" ማለት አይደለም:: ፈጠን-ፈጠን ብለን አንድ መፍትሄ ላይ በምርምር መድረስ እንችላለን:: እስከዛው ግን ጥያቄዎቹን አሁን በቀረቡበት መልክ መሰንዘርና አንዳንድ ተግባራዊ ነገሮችንም ማሰብና ከስር ከስር ከመንደርና ቀበሌያችን ጀምረን መፈፀምም አለብን:: ይህ ፅሁፍ፥ ሌላው ቢቀር፥ በምን አቅጣጫ ማሰብና ምን-ምን ከዛሬ ጀምሮ መተግበር እንዳለብን አንዳንድ ፍንጭ ሰጥቷል የሚል ተስፋ አለኝ::

ይብቃኝ!!!!! ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!

---

መጋቢት አጋማሽ ገደማ ተረቀቀ፥ ሚያዝያ 14/1997 ጥቂት ታደተ:: ሚያዝያ 15/1997 ግዮን ሆቴል "Reading Club" ላዘጋጀው ጉባዔ ይኸው ቀረበ:: ምን ይደረግ? ጊዜ የለም::